ህዳር 16 ቀን 2004 ዓ ·ም·

# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/

## ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ህዳር 16 ቀን 2004 ዓ ·ም· አዲስ አበባ በሚገኘው ዋናው ጽ/ቤት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ። መኢአድ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ በአባላቱና በደጋፊዎቹ ላይ እየደረሰ ስላለው ግድያ፣ እስራት፣ ድብደባ፣ ማስፈራራት፣ ከንብረትና ከመሬት መፈናቀል እንዲሁም ሌሎች አፈናና እንግልቶችን በመዘርዘር ገዥው ፓርቲ እያደረሰበት ያለውን ሰቆቃ አውግዟል።

በመግለጫው በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ በሚገኙ አባላቱ ላይ እየደረሰ ያለው ህገ ወጥ እርምጃ እንዳሳሰበውም ጠቁሟል። አያይዞም ምርጫ ቦርድ፣ ፖሊስ እና የደህንነት ኃይሉ እየፈጠሩበት ያለውን ጫናም እንዲያቆሙ አሳስቧል።

የመኢአድ ከፍተኛ አመራሮች እንደገለፁት ከተሻሻለው የፓርቲዎች የምዝገባ አዋጅ እና ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ምርጫ ቦርድ በፓርቲው ላይ እየፈጠረ ያለው ጫናና ጣልቃ ገብነት አግባብነት የሌለው ነው ሲሉ ኮንነዋል። ይህንን የምርጫ ቦርድ ህገ ወጥ አካሄድ ለማስቆም ለቦርዱ ተደጋጋሚ ደብዳቤ መፃፈቸውንም አስታውቀዋል።

በወቅቱ ከተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ለተነሱ ጥያቄዎች የአመራር አባላቱ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ፓርቲው በውስጡ የተፈጠሩ ውዥንብሮችን እያጠራ መሆኑን በመጠቆም የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ የህግና ሥነ ሥርዓት ቋሚ ኮሚቴ የአስተዳደርና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በማዋቀር ወደ ሥራ መገባቱን ገልጸዋል።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ገዥው ፓርቲ በገጠርም ሆነ በከተማ በአመራሮቹና በአባላቱ ላይ የሚፈጽመውን ከፍተኛ የሆነ ኢሰብአዊ ድርጊት ለማስቆም የኢትዮጵያ ህዝብና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ከጎኑ እንዲቆሙ ጥሪ አቅርቧል።

ጋዜጣዊ መግለጫውን ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የመኢአድ ፕሬዚዳንት፣ አቶ ወንድማገኝ ደነቀ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ዋና ጸሃፊ እና ወ/ት መሶበወርቅ ቀጣው የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ኃላፊ የሰጡ ሲሆን በቦታውም የግል ጋዜጦች፣ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን እና ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ተገኝተዋል።